# <u>በብሪታንያ የኢትዮጵያውያን ሕብረት ለፍትህ ተመሰረተ!!</u>

15 ጁላይ 2016

ኢትዮጵያ ሃገራችን ጥንታዊና የረጅም ግዜ ታሪክ ያላት፣ የሰው ልጅ መገኛ፣ የስልጣኔና የሰፊ ባህል መሰረት የሆነች ታላቅ ሃገር ናት። ህዝባችን ለነጻነቱ ያላሰለሰ ትግልን በማካሄድና ከፍተኛ መስዋእትነትን በመክፈል በዉጭ ወራሪዎች ላይ ድልን አስመዝግቦ ሃገራችን ለሌሎች አገራት ሳይቀር ምሳሌ እንድትሆን አድርጓታል:: ነገር ግን ባለፉት 25 ዓመታት ዘረኛውና ጠባቡ የወያኔ ቡድን በዘረጋው የአፓርታይድ ስርአት የተነሳ ህዝባችን አሰቃቂ ግፍና በደል እየተፈጸመበት ይገኛል። አገዛዙ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚፈፅመው ግፍ ፅዋው ሞልቶ በመፍሰሱ መሠረታዊና ሕገ-መንግሥታዊ መብትን የጠየቁ ዜጎች እጣ ፋንታ መታሰርና መሞት ወይንም ቀያቸዉን ለቀው ለአስከፊ ስደት መጋለጥ በመሆኑ ኢትዮጵያና ህዝብዋ ከመቸዉም ጊዜ በላይ ለከፍተኛ አደጋ ተጋልጠው ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት ፣ ፍትህና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ሃገር ለመመስረት ለዘመናት በፅኑ በመታገል መጠነ ሰፊ መስዋዕትነት የከፈለና ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት መመስረት ያለውን ብቃት ያስመሰከረ ቢሆንም፤ ይህን የሚመኘውን ራዕይ ተግባራዊ ለማድረግ እስካሁን አልተቻለውም። ለዚህ ራዕይ ያለመሳካት ዋንኛው ምክንያት በስልጣን ላይ ያለው የወያኔ አፋኝና የዘረኛ አገዛዝ ነው።

ሃገራችን የምትገኝበት አደገኛ ሁኔታ ያሳሰበንና በሀገራችን ነፃነትና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን የምንታገል በብሪታንያ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ላለፉት ጥቂት ወራቶች በተለያዩ ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ተከታታይ ስብሰባዎችን ካካሄድን በኋላ ቀጣይ ትግላችንን ፈር ለማስያዝ **“በብሪታንያ የኢትዮጵያውያን ሕብረት ለፍትህ”** የተባለውን አካል መስርተናል።

የዚህ አካል ዋና አላማ የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድና ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላማዊ ሽግግር ተደርጎ ሕዝባዊ ሥርዓት ለመገንባት በሚደረገው አገራዊ ትግል ዉስጥ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ኢትዮጵያውያንን በማቀራረብ፣ በማሰባሰብ፣ የምክክርና የመረጃ ልውውጥ በማድረግ በጋራ የሚያካሂዱትን የተጠኑና ውጤትን መሰረት ያደረጉ የትግል እንቅስቃሴዎችን በማቀድ፣ በማስተባበር፣ በመምራትና ሌሎች ተመሳሳይ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎችን በመርዳት ህልዉናዋ የተከበረ ሰላም የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንድትገነባና ዜጎቿ ፍትህና እኩልነት እንዲጎናጸፉ አስተዋጽኦ ማድረግ ነው።

አካሉ የተመሰረተው የሚከተሉትን ተጨባጭ ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው:-

- በሀገራችን ያለውን የፖለቲካ ቀውስ በመገንዘብና ባለፉት 25 ዓመታት ለነፃነትና ለፍትህ የተደረገውን ትግልና የተከፈለውን መስዋዕትነት በማጤን።
- በተናጠልና በተበታተነ ሁኔታ የሚደረግ ትግል የኢትዮጵያን ህዝብ ነጻነት፤ ፍትህና ዲሞክራሲ ከማጎናጸፍ ይልቅ ለአፋኝ ስርአቱ እድሜ መራዘም ምክንያት መሆኑን በመገንዘብ።
- ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አፋኝ ስርአት ብሶት በወለደው ሕዝባዊ እምቢተኝነትና ቁጣ መወገዱ የጊዜ ጉዳይ መሆኑ ግልጽ እየሆነ በመምጣቱ።
- የወያኔ ስርአት መወገድና በሕዝብ ፈቃድ ላይ ብቻ በተመሰረተ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት መተካቱ ለሃገራችን አንድነት ለመላው ሕዝቧ ሰላምና ብልጽግና እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በማመን።
- በሃገራችን ላይ እያንዣበበ ያለውን አደጋ ለመታደግ በሰፊው ተቃዋሚ ጎራ የተሰለፈ ሁሉ በመቻቻል፣ በመቀራረብ፣ በመመካከርና በአንድነት “ድር ቢያብር አንበሳ ያስር” የሚለዉን ጥንታዊ ጠቃሚ አባባል ግንዛቤ ዉስጥ ባስገባ መልኩ በህብረት ከመታገል ውጭ ሌላ አማራጭ የሌለው መሆኑ በመረዳት።

- ሁኔታዎች ወደ አልተፈለገ የፖለቲካ አቅጣጫ እንዳያመሩ፣ የሃገራችን አንድነት እንዳይናጋና የህዝባችን ደህንነት ቀውስ ዉስጥ እንዳይገባ በማሰብ ሲሆን:-

ሃገሪቱዋን ከተጋረጠባት አደጋ ለማዳን የሁሉም ችግሮች  ምንጭ የሆነውን የወያኔን ሁዋላ ቀር የዘረኛ ከፋፋይ ስርአት ከስሩ ነቅሎ መጣልና በምትኩም ዲሞክራሲያዊ ስርአትን መገንባት ለኢትዮጵያ ህዝብ የወደፊት እድገትና ደህንነት ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ ነው። ከሰርአቱ መወገድ በኋላም ቢሆን በማኅበረሰባችን አንድነትና በሃገራችን ሉኣላዊነት ላይ አደጋ እንዳይፈጠር ተደራጅቶና በጽናት ቆሞ መታገል አማራጭ የሌለው መፍትሂ ነው።

ህብረቱ አላማውን እውን ለማድረግ በነደፈው መርሃ ግብር መሰረት በመነሻነት በብርታኒያ የሚኖሩ ኢትዮጲያውያኖችን በማሰባሰብ ህዝባዊ መሰረት ለማስያዝ ቀጣይ እንቅስቃሴዎችን የሚያደርግ ሲሆን፣ በአጭር ጊዜም ህዝባዊ ስብሰባ በለንደን ከተማ እንደሚያዘጋጅ እየገለጽን ተያያዥ ዝርዝር መርሃግብሮችን ወደፊት የምናሳውቅ መሆኑን በትህትና  እንገልጻለን።

በዚህ አጋጣሚ በብሪታኒያ የምትገኙ ነጻነት ናፋቂ የሆናችሁ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ሕብረቱን በአባልነት ወይም በደጋፊነት በመቀላቀል ተሳትፎ እንድታደርጉ  ሃገራዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**የወያኔን አፓርታይድ ስርአት ከስሩ ነቅሎ ለመጣል በኢትዮጵያዊነት መደራጀትና በጽናት ቆሞ መታገል አማራጭ የሌለው መንገድ ነው!**

**በብርታኒያ የኢትዮጵያዉያን ሕብረት ለፍትህ**

**ሎንደን**

**ስልክ ቁጥር**: +44 07903448667 **ኢሜል**: eujb.london@gmail.com